# <u>የሌንጮ ለታ ዘረኛ ጫጫታ</u>

## <u>እውን ኢሕአፓ ነፍጠኛ?</u>

**ጫልቱ ዮሐንስ**

***ግም ለግም አብረህ አዝግም እንዲሉ የነሆለለና በቀቢፀ ተስፋ የተዋጠን አዛውንት ተከትለው አንጃ የሆኑ ጥቂቶች ኢትዮጵያን ባዕድ ሀገር ባዩን ዋና ዘረኛ ሌንጮ ለታን በእንግድነት ጋብዘው ለጠባብነት ጫጫታው መድረክ ከመስጠታቸው ሌላ በለመደበት ምላሱ አማራ የሚ ለውን የፈረደበት ሕዝብና ኢሕአፓንም በነፍጠኛነት ሊከስ ዕድል ሰጥተውታል።***

***ሌንጮ ለታ ማነው? ሌንጮ ለታና የወለጋ ምርጦችን በተመለከተ ዶክተር መረራ ጉዲና በቂ መረጃ ሰጥተውናል። የጊምቢና ነቀምቴ የሚሲዮኖች ተከታዮች የኦነግ መሪዎች ሆነው ስላደረሱት ጉዳት በሚገባ ገልጠዋልና ሁሉ ዜጋ ፅሁፋቸውን ዳግም ሊያነበው ይገባል። ሌንጮ ለታ ታሪኩ መደበቅ የሚገባው ነው። ለምን? አሳፋሪ ነውና። ሌንጮ ለታ በአፄው ዘመን ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ ሚና አልነበረውም። በደርግ ጊዜ ግን የደርግ ተለጣፊ ቡድን አባል ሆኖ ደርግ የኦሮሞ ሕዝብ ጥቅም አስከባሪ ነው ብለው በኢሕአፓ ላይ ይዘምቱ ከነበሩት አንዱ ነው። በዚህም መሰረት ነው የደርግ ተለጣፊ ሆኖ ሲሰራ የነበረው። ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ሲካሄድ ሌንጮ ደጋፊና ደርግ ነበር። እነ ገላሳ ዲልቦና ሌሎችም የተለየ ታሪክ አልነበራቸውም። በነገራችን ላይ ሌንጮ ለታ ዮሐንስ ለታ፣ ዲማ ነገዎ ዮሐንስ ነገዎ ወዘተ ነበር ስማቸው።እንደ ጥቁር አሜሪካኖች ነቃን ፀረ አማራ ሆንን ሲሉ ነው ጭንቅላት በመቀየር ፈንታ ስም የቀየሩት። ሌንጮ ለታ የእነ መኢሶን ፣ኢጭአት፣ማሌሬድ ወዘተ በደርግ ሲመቱ ፈርጥጦ ኦሮሚያ እስላሚያ የሚለው የሼክ ጃራ ፋሺስት ቡድን ጋ ተቀላቅሎ ነበር። ከባሮ ቱምሳ ጋር። በደርግ የተገደሉት የሬቨረንድ ጉዲና ቱምሳ ወንድም። ባሮ በዚሁ ግንባር ሲገደል ሌንጮ እንዴት ወደ ሶማሊያ እንደተሸኘና መገለፅ ያለበት ጉዳይ ነው ፡ ከገዳዮቹ ተባብሮ? እንዴት?***

***ሌንጮ ለታ ከሶማሊያ ወደ ሱዳን ዘልቆ ከሻዕቢያ ጋር ተያይዘው ኦነግ ከሚሉት ጋር ተደባልቆ (ኮበር አካባቢ ቢሮ) ቀይ ሽብሩ አማሮች በኦሮሞዎች ላይ ያካሄዱት ጭፍጨፋ ነው ብሎ እየፃፈ፣ ኢሕአፓ ትምክተኛ ነው ብሎ እየኮነነ፣ፀረ አማራውን ፕሮፓጋንዳ እየለፈፈ ቀጠለ ፡ ፡ ኦነግ ለነበረው ፅንፈኛ አቅዋም ሁሉ ዋና መሪ የነበረው ሌንጮ ዋና ተጠያቂ ነው። የሻዕቢያ ሎሌ ሆኖ ሌንጮ ለብዙ ዓመታት በፀረ አማራነት ወይም ፀረ ኢትዮጲያዊነት አገልግሏል።***

 ደርግ ሊወድቅ ሲል በለንደን የሰላም ጉባዔ ሲባልና ወያኔና ሻዕቢያ እነ ኢሕአፓ/ኢዴኃቅና ሌሎች አይገኙ ሲሉ ሌንጮ እሺ ብሎ ለንደን ተጉዞ በሽፋን ሰጪነት ደረጃ ካገለገለ በኋላ/ ሄርማን ኮኸን አላማከራቸውም/ በግድግዳ ላይ ያረፈ ዝንብ ነበርን ብሎ ሲያማርር ተደምጧል:: በወያኔ አዘጋጅነት በተካሄደው የሽግግር ጉባዔም ሌንጮ ለታ እጁን ቀስሮ የወያኔ ጦር የሽግግሩ መንግስቱ ጦር ይሁን ብሎ ድምፅ ሰጥቷል:: ወደ ኤርትራም ተጉዞ በኢትዮጵያ ስም ደማቸውን ያፈሰሱትን አውግዞ ለኢሳያስ አሽከርነቱን ገልጿል:: የኦነግ መሪዎች ከወያኔ ጋር አብረው መስራት ሲጀምሩም ዋናው ተዋኚ ሌንጮ ለታ ነበር:: በአማራው ሕዘብ ላይም ፀያፍ ዘመቻ አካሂዷል::

በበደኖ ጭፍጨፋ ሲካሄድ ሌንጮ ለታ ከቢሮው ሆኖ  በሏቸው ሲል ትዕዛዝ የሰጠ  ሰው ነው ለሚለው ክስም ሌንጮ በሚያሳምን ደረጃ ገና አላስተባበለም:: ኦነግ ከወያኔ ጋር የስልጣን ተጋሪ ሆኖ ከሲዳማ፤ አፋር፤ ጉራጌ፤ አማራ ወዘተ መናከስ በጀመረበተ ጊዜ (ደቡብንና ሐረር ን ያስታውሷል) ቀን ቀን ይተላላፍ የነበረው የኦሮሞ ራዲዮ ፕሮግራም ውስጥ ሌንጮ ከቀሪ ው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያለን ግንኙነት “ ሁላችንም የአዳም ልጆች መሆናችን ብቻ ነው” ሲል ከመደመጡ ባሻገር በመሀላችሁ ሆነው ቋንቋችሁን የሚናገሩትን (አማሮች) ተጠንቀቁ ብሎ ጥለቻና ግጭት ሲያራግብም  ነበር:: ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ደግሞ ወያኔ የኦነግን አመራር ሊያዋርድ ብሎ ከሀገር ውጡ በሚል የመውጫ ቪዛ ካተመላቸው በኋላ በኤርትራው አምባሳደር በኃይሌ መርቀሬዎስ አቅራቢነት ሌንጮና ዲማ ነገዎ መለስ ጋ ገብተው መሰናበ ታቸውንም መጥቀስ ይገባል? ሕዝብን ቢቀር አባላትን የሚያበሳጭ ድርጊት? ያ ሁሉ የኦሮሞ ልጅ ሲታገት ከወንጀለኛው ቤት ገብቶ መሰነባበት ምንስ ይባላል? በ1993 ለግዮን የሰላም ጉባዔ የመጡ ሲታሰሩም ሌንጮ ምንም እንደማይሆን በማወቅ አዲስ አበባ ሄዶ የሰራ ው ቲያትር ከአንጎላችን አይጠፋም:: ኢብሳ ጉተማ የተባለውን ላስፈታ መጣሁ ባለበት አፉ “ ከትምክህተኞቹ ጋር ስለታሰረ ” ብሎ በወያኔ የታገቱትን ሀገር ወዳዶች ሁሉ መዝለፉም የሚታወስ ነው:: “ትምክህተኛው” አበራ የማነአብ እስካሁን ታስሮ በቃሊቲ ሲገኝ ሌንጮ አንዴ ካናዳ አንዴ ኖርዌይ እያለ ከመለስ ጋርም እየተደማመጠ መኖሩን መጥቅስ ያስፈልጋል::

ኦነግ ቢያንስ በሶስት አንጃ ተከፍሎ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት ሌንጮ ለታ ቢያንስ ለመጨረሻው አንጃ መፈጠር ምክንያት መሆኑ ተገልጧል:: በዳውድ ኢብሳ የሚመራውን ኦነግ ለመጉዳት እየሰራ እያሴረ ነው የሚባለውም እንዲሁ አይደለም:: በርካታ ጊዜ ሌንጮ በኦስሎ ከወያኔዎች ጋር መነጋገሩም ምስጢር አይደለም:: በቅርቡ ደግሞ ሌንጮ ከዲማና አባ ቢያ ጋር በመሆን በአምስተርዳም ከተማ ከወያኔ አምባሰድርና ሌሎች ጋር ተገናኝቶ

ዕርቅን ማውራቱ ተዘግቧል። ይህ ከሕዝብ ጀርባ የሚሸረብ ሴራ ነው በሚል ኢሕአፓ ማጋለ ጡና ማውገዙ የሚያስመሰግነው ነው። ዘረኛው ሌንጮ ግን ኢሕአፓ በኦሮሞ ጉዳይ ምን አገ ባው ከማለቱ ሌላ ድርጅቱን በነፍጠኝነት ከሷል። የጠባብ ቋንቋው ቅንጣትም አልተቀየረ !! ሌንጮ ለመጣ ላለፈ አገዛዝ እየሰገደ በሕዝብ ላይ ሲሰየምና የስልጣን ትርፍራፊ ተመፅዋች ሲሆን ኢሕአፓ ፀረ ኦሮሞም ፀረ ኢትዮጵያም የሆኑትን አገዛዞች ታግሏል። ብዙ ጀግና ዴሞክራት የኦሮሞ ልጆችም በኢሕአፓነት ተሰውተዋል። ሌንጮና ጓደኞቹ ለስንቱ የኦሮሞ ልጅ መቀጠፍ ሃለፊነታቸውን ገና አላወራረዱም። ለሌንጮ ይህ ሀቅ ቢያመው አይፈረድበ ትም። ዛሬም ከወያኔ ሊታረቅና ፍርፋሪ ስልጣን ሊቀራመት ቋምጧልና። ኢሕአፓ ግን ለሕዝብ ሙሉ መብት የታገለና የሚታገልም በመሆኑ በእነ ሌንጮ ዓይነቶቹ መዘለፉ የሚጠ በቅ ነው። ሌንጮ ለታ ኤኤፈ ዲ ወይም ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የተባለውን የሻዕቢ ያ መሳሪያ ስብስብ ያፈረሰው ኢሕአፓ ነው ብሎ ከሷል። ከሆነ ኢሕአፓን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያመስግነዋል። የሻዕቢያን እንግዴ ልጅ ቀብሮልናልና!!

ለሌንጮ መድረክ ሰጥተው ድርጅትና ሰማዕትንና ኢትዮጵያን የሚያሰድቡት አንጃዎችም በሚያሳዝን ደረጃ እየቆሸሹ እንዳሉም ለመታዘብ በቅተናል። ከሌንጮ ጋር አብረው ወደ አዲስ አበባ ሊጓዙ ቢነሱ አይገርምም።